# መድብለ ጋብቻ ዝሙት ነውን?



ዐቅበተ ኢስላም ኑረዲን

## ማውጫ

መግቢያ ..... 3
የዝሙት ትርጓሜ ..... 4
መድብለ ጋብቻስ? ..... 5
መፅሀፍ ቅዱሳዊው አረዳድ ..... 5
ማህበረሰባዊ እውነታ ..... 7
ቀላሉ መፍትሔ ..... 11
ማጠቃለያ ..... 12

# መግቢያ

በአላህ ስም እጅግ አዛኝ እጅግ ሩህሩህ በሆነው። የአላህ ሰላምታና እዝነት በነቢያት መደምደሚያ በሆኑት በነቢዩ ሙሀመድ ላይ ይሁን።

እንደ ንፅፅር ተማሪና እንደ ዕቅበተ- እምነት አጥኚ በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉ አወዛጋቢ ርዕሶች አንዱ የመድብለ ጋብቻ እና ዝሙት ግንኙነት ነው። በጣም በርካታ ክርስቲያ ዕቅበተ እምነት አጥኚዎችም በፅንሰ ሀሳቡ ላይ አይስማሙም። ጥቂቶች ኦሪት ዘፍጥረት 2፡24ን[1] በመጥቀስ በግልፅ "በመፅሀፍ ቅዱስ መድብለ ጋብቻ ዝሙት ነው።" ሲሉ በርካቶች ደግሞ የተለያዩ ምክንያቶችንና ማስረጃዎችን በመጥቀስ "ዝሙት አይደለም" ይላሉ። እኔም እንደ አንድ የሀይማኖት ንፅፅር ተማሪ የጉዳዩን አንገብጋቢነት በመረዳት "መድብለ ጋብቻ፡ ንፅፅራዊ አቀራረብ" በሚለው ሰፊና ጥልቅ ጥናቴ በሰፊው ዳስሸዋለሁ። መፅሀፉ የህትመት ብርሃን እስኪያገኝ የንፅፅር ተማሪዎችና አጥኚዎች ፅንሰ-ሀሳቡን በሰፊው ይወያዩበትና ያጠኑት ዘንድ ከውቂያኖሱ ጠልቄ እንካችሁ ብያለሁ። በርዕሱ ላይ ለሚነሱ ውዥንብሮች በዚህ ፅሁፍ ምላሽ ለመስጠት አልሞከርኩም። ምክንያቴም በዋናው መፅሀፍ በተለያየ ቦታ የተጠቀሰ በመሆኑ አንባቢን ወደ ዋና መፅሀፍ ለማቅረብ ስለፈለኩ መሆኑን በቅንነት ተረዱት።

[1] የዚህንና ሌሎች በርካታ በመድብለ ጋብቻ ላይ የሚነሱ ብዥታዎችን "መድብለ ጋብቻ፡ ንፅፅራዊ አቀራረብ" በሚለው መፅሀፌ በሰፊው ዳስሻለሁ።

## ከአንድ በላይ ጋብቻ ዝሙት ነውን?

መድብለ ጋብቻ ዝሙት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ከማየታችን በፊት በመጽሀፍ ቅዱስ ዝሙት ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንመልከት።

## የዝሙት ትርጓሜ

በርካታ ጸሀፊዎች *"ዝሙት ማለት ከጋብቻ ውጭ የሚደረግ ማናቸውም ዓይነት የወሲብ ግንኙነት ነው"* (የመጽሀፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡ ገጽ 217) ቢሉም ከመጽሀፍ ቅዱስ አንጻር ይህ ትርጉም ትክክል እንዳልሆነ በርካታ የክርስቲያን ጸሀፊዎች ይገልጻሉ። በመጽሀፉ በዝሙት ምክንያት የተወቀሱት በሙሉ ካገባች ሴት ጋር ግንኙነት የፈጸሙ ብቻ ናቸው። በመጽሀፍ ቅዱስም "ባል ባላት ሴት ማንም እንዳያመነዝር ከአብርሃም ቃላት አባቱ ያዕቆብ አባቱ ያነበበላቸውን ነገሮች አሰበ።" (መጽሀፈ ኩፋሌ 27:24) የሚል ተጽፏል። ካላገባች ሴት ጋር አግብተውም ይሁን ሳያገቡ ግንኙነት የፈጸሙ ግን በአንድም ቦታ ዝሙት ፈጽመዋል አልተባሉም። የመጽሀፍ ቅዱስ አጥኚዎች በመጽሀፉ የሚገኙ ማስረጃዎችን በአንድ ላይ በማሰባጠር የክርስትና የጋብቻና የዝሙት ትርጓሜን እንደሚከተለው በጥቅል ከፋፍለው አስቀምጠዋል።

i, ያላገባ ወንድ ከአገባች ሴት ጋር ግንኙነት ሲፈጽም — ግንኙነቱ ዝሙት ይሆናል።

(ትንቢተ ሕዝቅኤል 16:32) (ኦሪት ዘሌዋውያን 20:10) (ኦሪት ዘዳግም 22:22-24)(ወደ ሮሜ ሰዎች 7:3) (1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 7:39) አንቀጾቹ ያገባንም ያላገባንም ወንድ ያመለክታሉ።

ii, ያገባ ወንድ ከአገባች ሴት ጋር ግንኙነት ሲፈጽም — ግንኙነቱ ዝሙት ይሆናል።

(ዘፍጥረት 20:1-7) (መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 11:1-27)

iii, ያላገባ ወንድ ካላገባች ሴት ጋር ግንኙነት ካደረገ — ግንኙነቱ ጋብቻ ይሆናል።

(ኦሪት ዘዳግም 22:28-29) (ኦሪት ዘጸአት 22:16-17)

iv, ያገባ ወንድ ካላገባች ሴት ጋር ግንኙነት ካደረገ — ግንኙነቱ ጋብቻ ይሆናል።

(ዘጸአት 21:10)

ከዚህ የምንረዳው በመጽሀፍ ቅዱስ ዝሙት የሚባለው ያገባም ይሁን ያላገባ ወንድ ከሌላ ሰው ሚስት (an other man's wife) ጋር ግንኙነት ሲኖረው ነው። (E Boyd and Kendra Daniels፡ Polygyny According to the word of Yahovah፡ Pp. 7-8)

## መድብለ ጋብቻስ?

ወደ መድብለ ጋብቻም ስንመለስ አንዳንድ ጸሀፊዎች ከአንድ በላይ ማግባት ዝሙት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ዲያቆን ኤፍሬም የኔሰው "የጋብቻ ሕይወትና የሩካቤ ሥርዓት" በሚል ርዕስ በማህበራዊ ድህረ ገጾች ላይ በተከታታይ በጻፈው ጽሁፉ በዓለማችን (በክርስቲያኖች መካከል) የተንሰራፉትን የዝሙት መንገዶች ሲዘረዝር *"ከአንድ በላይ የትዳር አጋር መያዝ"* አንዱ እንደሆነ ጠቅሷል፡፡ (ክፍል፡ ፪) ሲታዊያን መነኮሳት የተሰኘ ድህረ-ገጽም *"ከሕጋዊ ሚስቱ ተለይቶ ሌላ ሴት የሚያገባ ባል አመንዝራ ነው፤ ምክንያቱም ሌላ ሴት ከእርሱ ጋር ዝሙት እንድትፈጽም አድርጓልና፤ ከእርሱ ጋር የምትኖር ሴትም ዘማዊት ናት፣ ምክንያቱም የሌላን ባል ለራሷ አድርጋለችና፡፡"* በማለት ከአንድ በላይ ጋብቻ ዘማዊነት እንደሆነ ጽፏል፡፡

## መፅሀፍ ቅዱሳዊው አረዳድ

ይህ ግን የተሳሳተ ግንዛቤ ነው፡፡ ለዚህ በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ ቢቻልም የተወሰኑትን ብቻ አስቀምጣለሁ፡፡

፩, ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ዝሙት ማለት ካገባች ሴት ጋር የሚደረግ ግንኙት እንጂ ያገባ ወንድ ከብዙ ሴቶች ጋር የሚያደርገው ግንኙት አይደለም፡፡ መጽሀፍ ቅዱስም ዝሙት ነው አላለም፡፡ ከላይ በሊቃውንቱ በቀረቡት የጋብቻና የዝሙት ህግጋት መሰረት ዝሙት የሚሆነው አንድ ሴት ከአንድ በላይ ወንዶችን ስታገባ (polyandy) ሲሆን አንድ ሰው ከአንድ በላይ ሴቶችን ማግባቱ (polygany) ከዝሙት የተቆጠረበት አንድም አንቀጽ የለም፡፡

፪, መጽሀፍ ቅዱስ በብዙ ቦታዎች ላይ እንዳስቀመጠው ዝሙት ይቅር የማይባል ከባድ ወንጀል ነው፡፡ በሙሴ ጽላት ላይ ከተከተቡት የእግዚአብሔር ትዕዛዛት አንዱ ነው "አታመንዝር፡፡" (ኦሪት ዘጸአት 20:14) መጽሀፍ ቅዱስ "ማናቸውም ሰው ከሌላ ሰው ሚስት ጋር ተኝቶ ቢገኝ፥ አመንዝራውና አመንዝራይቱ ሁለታቸው ይሙቱ፤ እንዲሁም ክፉውን ነገር ከእስራኤል ታስወግዳለህ፡፡ " (ኦሪት ዘዳግም 22:22) በሌላ አንቀጽም "ማናቸውም ሰው ከሌላ ሰው ሚስት ወይም ከባልንጀራው ሚስት ጋር ቢያመነዝር **አመንዝራውና አመንዝራይቱ ፈጽመው ይገደሉ**፡፡" (ኦሪት ዘሌዋውያን 20:10) በማለት የዝሙት ማስተሰሪያው ከባድ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ስለ ዝሙተኞችም "ከሴት ጋር የሚያመነዝር ግን አእምሮው የጎደለ ነው፤ እንዲሁም የሚያደርግ ነፍሱን ያጠፋል፡፡" (መጽሐፈ ምሳሌ 6:32) በማለት ዝሙትን ትክክለኛ አዕምሮ ያለው ሰው እንደማይፈጽመው ይናገራል፡፡ ምንም ይሁን ማን ዝሙት እስከፈጸመ ድረስ ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፡- እግዚአብሔር "እንደ ልቤ" ያለው ንጉስ ዳዊት ከኦሪዮ ሚስት በዝሙት የወለደው ልጅ በጠና ታሞ እንደሞተ መጽሀፉ ይገልጻል፡፡ (2 ሳሙኤል 12፡15) እግዚአብሔር የዳዊት ልጅ ነውና ልለፈው አላለም፡፡ እግዚአብሔር ዝሙት የፈጸመው ሰው ነብይም ይሁን ጻድቅ በፍጹም አይምርም፡፡ ነገር ግን በርካታ ነብያትና ጻድቃን ከአንድ በላይ ሚስት አግብተዋል፡፡ እግዚአብሔርም ይህንን ተግባራቸውን ፈጽሞ አልነቀፈም፡፡ ይህን ድርጊታቸውንም በዝምታም አልፎታል፡፡ ይህም ከአንድ በላይ ጋብች ፈጽሞ ዝሙት እንዳልሆነ ያሳያል፡፡ "ከአንድ በላይ ጋብቻ ዝሙት ነው" የሚለው አስተሳሰብ *"እግዚአብሔር ዝሙትን (አመንዝራነትን) በዝምታ አልፎታል"* የሚለውን ስለሚያመለክት ከመጽሀፉ ጋር የተጋጨ ሀሳብ ነው፡፡ በተመሳሳይም በመጽሀፉ የግድያ ፍርድ የተጣለበት ዝሙት ወይም አመንዝራነት እንጂ በአንድም ቦታ

ከአንድ በላይ ማግባት የግድያ ፍርድ እንደተሰጠው የሚጠቁም አንድም አንቀጽ የለም። ይህም በመጽሀፍ ቅዱስ ከአንድ በላይ ጋብቻ ፈጽሞ ዝሙት እንዳልሆነ ያመለክታል።

፫, ከአንድ በላይ ጋብቻ ዝሙት እንዳልሆነ የሚያሳየው ሌላው ነጥብ ከላይ እንዳየነው እግዚአብሔር ለዳዊት በርካታ ሚስቶችን መስጠቱና ዳዊት ዝሙት ሲፈጽም መውቀሱ ነው። እግዚአብሔር ለዳዊት በርካታ ሚስቶችን ቢሰጠውም ዳዊት ግን ከባለ ትዳር ሴት ጋር ዝሙት በመፈጸሙ እግዚአብሔር ተቆጥቶበታል። ቁጣው ግን በዝሙቱ ምክንያት ስለነበር ቀድሞ በርካታ ሚስቶችን እንደሰጠው ካወሳ በኋላ "ይህም ሁሉ አንሶህ ቢሆን ኖሮ ከዚህ በላይ ጨምሬ በሰጠሁህ ነበር።" (2 ሳሙኤል 12:8) (NIV) በማለት ተጨማሪ ሚስቶችን ሊሰጠው እንደሚችል ተናግሯል። ይህም ከአንድ በላይ ጋብቻ ፈጽሞ ዝሙት እንዳልሆነና በእግዚአብሔር ዘንድም የተፈቀደ እንደሆነ ግልጽ ያደርጋል።

፬, አንዳንድ ክርስቲያን ጸሀፊዎች ከአንድ በላይ ጋብቻ ዝሙት እንዳልሆነ ለየት ባለ መልኩ ለማስረዳት ይሞክራሉ። ይኼውም የብሉይ ኪዳን መጽሀፍትንና የወንጌላዊያንን ትምህርት ያጠናው ጳውሎስ "ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆን ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም <u>አመንዝሮች</u> ወይም ቀላጮች ወይም <u>ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ</u> ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች <u>የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም</u>።" (1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 6:9-10) "ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ <u>ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል</u>።" (1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 6:18) "መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ <u>ሴሰኞችንና አመንዝሮችን</u> ግን <u>እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል</u>።" (ወደ ዕብራውያን 13:4) በማለት የላከውን መልዕክቶች በማጣቀስ "*ጳውሎስ ዝሙተኞች መንግስተ ሰማይ አይገቡም ብሏል፤ እነ አብረሃም ያዕቆብ ዳዊትና የመሳሰሉት ደግሞ መንግስተ ሰማይ እንደሚገቡ የተረጋገጠ ነው። ሆኖም እነዚህ ቅዱሳን ከአንድ በላይ አግብተዋል፤ ስለዚህ ከአንድ በላይ ጋብቻ ከዝሙት አይቆጠርም።*" ይላሉ። ዊልበር ኦዶኖቫን መጽሀፍ ቅዱሳዊ ክርስትና በአፍሪካዊያን ዕይታ በሚለውና ግርማዊ ቡሽ በተረጎመው መጽሀፉ ከአንድ በላይ ጋብቻ ዝሙት እንዳልሆነ ይገልጻል። (ገጽ 397) ማክስ ሞደርም Polygamy ... Is It Wrong? በሚለው አጭር ጥናቱ "*ምንም እንኳን ተስማሚው ጋብቻ አንድ ወንድ ለአንድ ሴት ቢሆንም በእስራኤላዊያን ዘንድ ሁለት ሚስት ማግባት እንደ ወንጀል ተቆጥሮ አልተወገዘም። በመጽሀፉ የተወሰኑ ታዋቂ ሰዎች ከአንድ በላይ ሚስት አግብተዋል። እነዚህ ሰዎች ደግሞ ወንጀለኛ ናቸው ተብለው እንዳልተወገዙ ይታወቃል።*" በማለት የተወሰኑ ከአንድ በላይ ያገቡ የመጽሀፉ ሰዎችን ይጠቅሳል። (ገጽ 2)

፭, ድርብ ጋብቻ ዝሙት እንዳልሆነ ከሚቀርቡት ማስረጃዎች አንዱ እግዚአብሔር ከአንድ በላይ ለማግባት መስፈርት ማስቀመጡ ነው። መጽሀፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ሁለት እህትማማቾችን በአንድ ጊዜ ማግባት አይቻልም፣ ከአንድ በላይ ያገባ ወንድ በሁሉም ሚስቶቹ መካከል ፍትህን ማስፈር አለበት፡ ወዘተ ...። ከአንድ በላይ ጋብቻ ዝሙት ቢሆን ኖሮ እነዚህ ህጎች ባላስፈለጉ ነበር። ከላይ አብራርተን እንዳየነው እግዚአብሔር ራሱ በርካታ ሚስቶችን ይሰጥም ነበር።

# ማህበረሰባዊ እውነታ

የሆነው ሆኖ ከአንድ በላይ ጋብቻን በመከልከሏ ቤተ ክርስቲያን ምን አተረፈች? ብለን ዓለማችንን ብንቃኛት የምናገኘው እውነት በጣም አስደንጋጭ ነው።

i, በተለይ በክርስቲያኑ ማህበረሰብ ውስጥ ሌዝቢያዊነት ተስፋፍቷል። በቄሶች ሙሉ ፈቃድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚጋቡት ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ሴቶች በጣም ብዙ ናቸው። ይህ ልንደብቀው የማንችለውና በርካታ የክርስቲያን ሰባኪዎች አጀንዳቸው አድርገው እያስተማሩበት ያለ ርዕስ ነው። ዲ. ሄኖክ ሀይሌም ተመሳሳይ ጋብቻን የሚያስፈጽሙ ቤተ-ክርስቲያናት መኖራቸውን ጠቁሟል። (ክብረ ክህነት፡ ገጽ 26) ይህ የሆነው በባል እጥረት ምክንያትና "ታማኝ የወንድ ጓደኛ" ባለማግኘታቸው እንደሆነ ብዙዎች ይናገራሉ። ለሁሉቱም ችግሮች መፍትሔው ደግሞ ከአንድ በላይ ጋብቻ መሆኑ ጥርጥር የለውም። ዓለም ትገርማለች፡ ለግብረሰዶማዊያን የጋብቻ ፍቃድ ሰጥተው በሁሉም የሀይማኖት መጽሀፍት ፍቃድ የተሰጠውን መድብለ ጋብቻ ግን በህግ ከልክለዋል። ከአንድ በላይ ጋብቻ በእግዚአብሔር ዘንድ ወንጀል የተቆጠረበት አንዲት አንቀጽ ከመጽሀፉ ማግኘት አይቻልም። ግብረ-ሰዶማዊነት ግን ከከባድ ወንጀሎች ተቆጥሯል። ዓለማችን ግን በተቃራኒው እየተጓዘች ነው። የሀገራችን ሰባኪዎችም ከዐለማችን ጋር አብረው በመጓዝ ላይ ናቸው። ግብረ-ሶዶማዊነትን ለመከላከል ከሚያወጡት ጉልበትና ሀብት በላይ መድብለ ጋብቻን ለማጠልሸት የሚያወጡት ይበልጣል። RIP በቁማቸው ለሞቱ የሀገራችን ክርስቲያን ሰባኪዎች።

ii, በምዕመናኑ ዘንድ ዝሞተኝነት (አመንዝራነት) በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፋ መምጣቱ እንዳስጨነቃቸው በጽሁፍም በድምጽም ሰባኪያን እየገለጹ ነው። ዊልበር ኦዶኖቫን *"ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት ህጋዊ ባልሆነባቸው አውሮፓና ስሰሜን አሜሪካ ዝሙትና አመንዝራነት ወደ ፍች ይመራቸዋል። ብዙውን ጊዜ የተፋቱ ሰዎች ከዝሙት ሸሪኮቻቸው ጋር ይጋባሉ።"* አለፍ ብሎም ይህ አመንዝራነት ከመድብለ ጋብቻ እንደሚከፋም ተናግሯል። (መጽሀፍ ቅዱሳዊ ክርስትና፡ ገጽ 116) ከምዕራቡ ዓለም ጀምሮ ዓለማችንን እያመሳት ያለው ዝሙት በተለይ በወጣቶች ላይና በባለ ትዳር ወንዶች ላይ በስፋት ይታያል። ዲያቆን ኤፍሬምም *"ጓደኛ በሚል ሰበብ አንድ ወንድ የብዙ ሴቶች ባል፡ አንድ ሴትም የብዙ ወንዶች ሚስት የሚሆኑበት አጋጣሚ ተለምዷል። በተለይ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሚገኙባቸው አካባቢዎች ግብረ ዝሙት እየተስፋፋ ይገኛል።"* በማለት በምዕመናኑ ዘንድ ምን ያክል ዝሙታዊነት እንደተስፋፋ ይገልጻል። (የጋብቻ ሕይዎት እና የሩካቤ ሥርዓት፡ ክፍል ፮) የጭፈራ ቤቶችና ሴተኛ አዳሪዎች ደምበኞችም እነዚሁ ባለትዳሮች ናቸው። በርካታ የክርስቲያን ሰባኪዎችም ይህንኑ አፍ አውጥተው ለማስተማር ተገደዋል። ዲያቆን ኤፍሬምም ይህንኑ እውነት *"ከጣሊያን ወረራ ጊዜ ጀምሮ በሀገራችን እንደተስፋፋ የሚነገርለት የሴተኛ አዳሪነት ልማድ ባለ ትዳሮችን ጨምሮ የበርካታ ወጣቶች ሕይዎት እየበከለ ይገኛል።"* በማለት ጽፏል። (ዝኒ ከማሁ) እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የማይታወቀው የወንድ ጓደኛና የሴት ጓደኛም ሀገራችንን የዝሙት መናህሪያ አድርጓታል። አንድ ወንድ አንድ ሚስት ያገባል ነገር ግን በርካታ "የሴት ጓደኞችን" ይይዛል። ይህ ደግሞ ከአንድ በላይ ከማግባትም በላይ ነው። ምክንያቱም ከዚህ ግንኙነት በድብቅ የሚወለዱና በአባታቸው የተከዱ በርካታ ልጆች እንዲወለዱ ያደርጋለና። ኢትዮጵካሊክ በተሰኘ የሬድዮ ፕሮግራም ትዳር ካለው ወንድ በድብቅ ልጅ ወልደናል ያሉ ሴቶች ወደ ፕሮግራሙ ሲደውሉ በተደጋጋሚ ሰምተናል። በሀገራችን ባሉ ዩኒቨርስቲዎችም "ሹገር ዳዲ" ተብለው መኪና ይዘው ከግቢው በር ላይ ሴቶችን የሚወስዱት ባለትዳርና "የተከበሩ" የሚባሉ ሰዎች ናቸው። ይህም ሴት ተማሪዎችን ላልተፈለገ

እርግዝና እና ለውርጃ እየዳረጋቸው እንደሚገኝ በርካታ ጥናቶች ያሳያሉ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ማታ ማታ የሚያስጨፍሩና ጧት ጧት መዝሙር የሚከፍቱ መጠጥ ቤቶችን ቁጥራቸው ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ይገኛል። መንፈሳዊ አደጋዎች የሚል የትርጉም መጽሀፍ ጋና ውስጥ ስለሚካሄድ ይፋዊ ከአንድ በላይ ማግባትን እንዲህ ያስቃኘናል፡- *"ጋና ውስጥ 'ይፋ የሆነ' ከአንድ በላይ ማግባት አለ፡ ይኼውም፡ አንድ ባል ሁለት ሶስት ሚስቶች አሉት ማለት ነው። ነገር ግን በጋና ውስጥ በርካታ ስኬታማ የሆኑ ሰዎች የሚያደርጉት 'ይፋ ያልሆነ" ዓይነት ከአንድ በላይ ማግባት ደግሞ አለ። ከመንግስት ጋር ለተያያዙ ጉዳዮች ይዘዋቸው የሚሄዱና በህዝብ ፊት አብረዋቸው የሚታዩ አንድ የይፋ ሚስት አሏቸው። በነዚህ ሰዎች ህይዎት ውስጥ ይፋ ያልሆኑ ሴቶች ደግሞ አሉ። ይህም ደግሞ በህብረተሰባችን ውስጥ 'ወሳኝ ሰዎች' በሚባሉት ዘንድ የሚዘወተር ልማድ ነው። እንዲህ ያሉ ሰዎች ሚስቶቻቸውን የመፍታት ምንም ዓይነት ዕቅድ የላቸውም። የሳምንቱን የእረፍት ቀናት ከነዚህ የጎን ሴቶች ጋር 'ልዩ' ቦታዎች በመሄድ ያሳልፋሉ።"* (መንፈሳዊ አደጋዎች፡ ዳግ ሂዋርድ ሚልስ (ትርጉም)) ይህ የዓለማችንም የሀገራችንም እውነታ ነው።

iii, ይህ የቤተ ክርስቲያን ከአንድ በላይ ጋብቻን መከልከል ዝሙተኛ አስተማሪዎች እንዲፈለፈሉ ምክንያት ሆኗል። ምንም እንኳን ሁሉም ቤተ-ክርስቲያናት የዝሙትን አስከፊነት ቢያስተምሩም ከድሮም ጀምሮ የዝሙት ሰለባዎቹ ራሳቸው አስተማሪዎቹና አገልጋዮቹ ናቸው። ቤተ-ክርስቲያንን በማጥፋቷ ስሟ በክፉ የሚነሳው ንግስት ዮዲት ጉዲት ምንም እንኳ ታሪኳ አከራካሪ ቢሆንም ስለሷ ከተጻፉት ታሪኮች አንዱ የካህናቱን አመንዝራነት የሚያመለክት ነው። ያሬድ ሽፈራው ዶር. ሲሳይን በማጣቀስ ዮዲት የዕለት ምግብ ችግሯት ዝሙት ስትሰራ አንድ ካህን ከእርሷ ጋር በፍቅር ወድቆ አብርሃና አጽብሃ ካሰሩት የወርቅ መጋረጃ በእግሯ ልክ ቆርጦ ስጦታ በመስጠት ከእርሷ ጋር እንደዘሞተ። በዚህም ምክንያት ጡቷን እንደቆረጧት ጽፏል። (ከኢትዮጵያ ታሪክ የቱን እንመን? ገጽ 230-231) በባህሩ ዘውዴ መጽሀፍ ላይ እንደተጠቀሰው የአጼ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕል ጸሀፊ አለቃ ዘነበ እንዲህ ይላሉ *"ቀን ቀን የሰውን ስራ ይሰራሉ የእየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰብካሉ የሚሰማቸው የለም። ሌት ከጋለሞታ ጋር ያድራሉ።"* (የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983፡ ገጽ 36) በማለት የመምህራኑን የሌት ስራ ይነግሩናል። በውቀቱ ስዩምም ከአሜን ባሻገር በተሰኘ መጽሀፉ ያዕቆብ ብሩስ የተባለ ተጓዥ በማጣቀስ አቃቤ ሰዓት አባ ሰላማ ስለሚባሉ ቄስ ታሪክ *"(ሰላማ) በቤተ-ክርስቲያን በሶስተኛ እርከን ስልጣን አለው። በጣም ሀብታምና በጣም እኩይ ሰው ነው። <u>በጎንደር ውስጥ ከሰባ በላይ ቅምጦች እንደነበሩት</u> ይነገራል። ሴት የሚያማልልበት መንገድ የተማላዮችን ብዛት ያክል ያስደንቃል። <u>እንዲትን ሴት በፈለገ ቁጥር በግዝት ያስፈራራታል</u>።"* በማለት አስነብቦናል። (ገጽ 92) የአለቃ ገብረ ሀና ታሪክም "የሊቃውንቱን" የዝሙት ጥማት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ከአንድ በላይ ሚስት ካገባ ሰው በላይ አለቃ ገብርሀና ከብዙ ሴቶች ጋር ሲዳሩ ነው የምናውቃቸው። ብዙ ሚስት ያገባ ሰው በሚስቶቹ ይወሰናል ሆኖም አለቃ በሄዱበት ሁሉ መዳራት ያምራቸዋል። የአለቃን ሴሰኝነት የቤተ-ክርስቲያኗ ሰዎችም አልካዱም። "ዋናዎቻችንን እናስብ" በሚል በአለቃ ታሪክ መዘክር ላይ መጋቢ ሀዲስ እሸቱ አለማየሁ *"በእርግጥ አለቃ ሴት እንደማይምሩ ይታወቃል።"* በማለት ታዳሚውን ፈገግ አድርጓል።

ለዚህም ነው በውቀቱ ስዩም

*"በታሪክ ሜዳ ላይ*
*አሉላ ጎበና*
*ወንዱን አስከትለው ሲገድሉ ሲሞቱ*

*አባ ገብረ ሐና*
*እርስዎ ባይኖሩ ምን ይውጠው ሴቱ?"*
በማለት የተቀኘው። (ስብስብ ግጥሞች፡ ገጽ 109-111 ይመልከቱ!)
መዘክር ግርማም

"እና ቀሚስ የሚገልጡ፤
አባ ገብረሐና ነበሩ፣
ለፍትወት እንዳይመኙሽ ፈሩ፣ ..."

በማለት ሴሰኝነታቸውን ሸንቁጦ አልፏል። (አንድ ልጅ አዝማሪ፡ መዘክር ግርማ፡ ገፅ 20)

ባለንበት ዘመንም ይህ የመምህራኑ አመንዝራነት ጨመረ እንጂ አልቀነሰም። በርካታ የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደሮችና መምህራን የቤተ ክርስቲያኗን አማኞች የዝሙት መወጫ እያደረጓቸው እንደሆነ ሚዲያዎች ሁሉ ይዘግባሉ። "እዚህ ቦታ የምትገኝ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆነው ፓስተር እከሌ ይሄንን ያክል ሴት አማኞችን አስረገዘ" የሚሉ ዜናዎች የማህበራዊ ሚዲያ የዘወትር ወጎች ናቸው። ለምሳሌ፡- አንድ የናይጀሪያ ፓስተር በመንፈስ ቅዱስ ታዝዤ ነው በማለት 20 ሴቶች እንዳስረገዘ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ሲናፈስ ቆይቷል። (www.dailymail.co.uk%2Fnews%2Farticle-2979585%2FNigerian-pastor-arrested-impregnating-20-women-church-claims-God-commanded-sex-daughters.html%3Ffbclid%3DIwAR1T8flJ2xKwJDy0-jYnCtyyHUCpDlcLejRJqaZWcyyVfBeeeZHvwQ_YluE&h=AT2xi1mnEqBp14MQ6k_ElrNcpXbDHpkUBzhTy075ILMi7exFCb5WAwvrlK6Qa5ylSuRmWOMYl39XYZxiy4Hl9iOg9fPS4lSH6MILdsRTqNbk1hXqLnw_ZGP48q6l1d2u19PcQ0EwUo75BD_Iw) አንዳንድ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ትእዛዝ አስቼጋሪ ነው። የሀያ ሴቶችን ህይዎት እንዲያበላሹም ያዛል። በሀገረ ፖላንድም በሁለት አመት ውስጥ 368 የወሲብ ጥቃት በቀሳውስቱ ተፈፅሟል። ለዚህም ጥፋት በፍርድ ቤት ሲጠየቁ *"እንኳን እኛ ነብያት እና ልጆቻቸው እንኳን ሀጢያት ስርተዋል ስለዚህ እኛም ብንሳሳት ምን ይገርማል"* የሚል ምላሽ መስጠታቸው ተዘግቧል። በሀገረ ፈረንሳይ በባለፉት 70 ዓመታት ውስጥ በካቶሊክ ቄሶች 216 ሺህ ያህል ተጎጅዎች የወሲባዊ ጥቃት ሰለባ መሆናቸው አንድ ምርመራ እንዳጋለጠ BBC ዘግቧል።(https://www.bbc.com/amharic/news-58799029?at_custom3=BBC+News+Amharic&at_campaign=64&at_custom1=%5Bpost+type%5D&at_custom4=E2ED4D3C25C411EC8DA5E6D9BDCD475E&at_custom2=facebook_page&at_medium=custom7&fbclid=IwAR0ZND2LlWlFtNt_e2ukHMXvcrFuWDXql5q1duToa9WBalHhmiwn51EdkvM) አሻም TV "ፓስተሮቹ" በሚል በለቀቀው የወሬ መረጃ ፕሮግራም ላይ የዘመናችን በርካታ ፓስተሮች በ"እንፈውሳለን" ስም ታዳሚያን ፊት ለደቂቃዎች የወጣት ምዕመናንን ከንፈር እንደሚስሙና የተለያዩ ጾታዊ ትንኮሳዎችን እንደሚያደርጉ ብሎም የውስጥ ልብሶቻቸውን ሁሉ እንደያሶልቋቸው በምስል በማስደገፍ ተንትኗል። አንዳንድ ፓስተሮች እንደውም *"በዘር ፍሬዬ እንድፈውስ ታዝዣለሁ"* በማለት ለአምልኮ የመጡትን ምዕመናን እንደሚዳሩ አሻም አውርቶናል። በርግጥ እንደ ደቪድ ኮሬሽ ያሉና "የሁላችሁም ሚስቶችና ልጆች የኔ ናቸው" በማለት የምዕመናኖችን ሚስትና ሴት ልጆችን ለራሱ የወሰደ ዝሙተኛን በውስጣቸው አስቀምጠው ከአንድ በላይ ማግባት ክልክል ነው ከሚሉን በላይ አዕምሮው የተቃወሰ ሰው የለም። ለነገሩ ማንም ተራ አማኝ ብድግ ብሎ ነብይ ነኝ፡ ሀዋሪያ ነኝ፡ ትንቢት እናገራለሁ፡ እፈውሳለሁ ... በሚልበትና ምዕመናኑን ሳር በሚያስግጥበት እምነት ውስጥ ዝሙት ተራ ነገር ነው። መምህር ጽጌ ስጦታው ይነጋል በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሀፉ ከማህበረ ቅዱሳን

መስራቾች አንዷ የሆነችው በዛር መንፈስ የተጠቃችና ዛሩም "እንደ ማሪያም ነኝ እንደ ገብርኤል ነኝ" በማለት ለአባላቱ የተለያዩ ትዕዛዞችን ይሰጥ እንደነበር ጽፏል። ማህበሩ ሶስት ወንዶችና አስር ሴቶችን ያቀፈ ቢሆንም ሁለቱ ወንዶች በተለያዩ ምክንያቶች ከአባልነቱ ርቀዋል። በማህበሩ የቀረው የዛሩ ልዩ አገልጋይና ቃል ተቀባይ አንድ ዲያቆን ብቻ ነበር። ከእለታት በአንዱ ቀንም *"የዛሩ መንፈስ ወረደና እኔ ማሪያም ነኝ የማዛችሁን ሁሉ ማድረግ አለባችሁ አትጠራጠሩ ጥርጣሬ የመናፍቃን ባህሪ ነው እናም የማዛችሁን ሁሉ በእምነት አድርጉት በማለት ከወድሁ ለነገሩ ክብደትን ይሰጣል። በማስከተልም 'ድንግልናችሁ በተአምር የጋብቻችሁ ዕለት ይመለስላችኋል አሁን ግን ለዲያቆኑ ድንግልናችሁን ስጡት' ይባላሉ። እነርሱም ይህንን ያዘዘችው እመቤታችን ሆነችና ለታዘዘለት ዲያቆን ድንግልናቸውን ለመስጠት ወረፋ ተመዘገቡ። ... ዲያቆኑም ድንግልናቸውን ለመገርሰስ የተመዘገቡትን ልጃገረዶች ቅደም ተከተሉን በመጠበቅ የአራቱን ሴቶች ድንግልና ወሰደ ከዚያ በኋላ ግን ዲያቆኑ ኩራት ኩራት ተሰማውና የሌሎቹን ሴቶች ድንግልና ለመውሰድ ቀጠሮ በማራዘም አዘገያቸው። በእርግጥ ከእርሱ እንደማያመልጡና የታዘዙትም ለእርሱ እንደሆነ አስረግጦ ስለሚያውቅ ሊኮራ ይገባዋል።"* ( ገጽ 123-127) ቀጥሎም የልጆቹን ድንግልና የወሰደው ዲያቆን *"የሐመር መጽሄት ዋና አዘጋጅ ሆኖ ዲያቆን እሸቱ እያለ ስሙን መጻፍ ጀመረ። አሁን ደግሞ ቄስ ሆኖ በመስቀል ያሳልማል።"* (ገጽ 129) (ዲያቆን ሙሉጌታ ወ/ገብርኤል፡ ማህበረ-ቅዱሳን ወይስ ማህበረ- ሰይጣን፡ ገጽ 10-16) በማለት የሚዘገንን የዝሙት ታሪክ ነግሮናል። ወሸሂደ ሻሂዱን ሚን አህሊሀ ይልሀል ይህ ነው። ይህ ቄስ አስር ልጃገረዶችን አረከሰ። ይህ ታሪክ ከታዋቂ ሙስሊሞች በአንዱ ላይ ቢገኝ የማህበሩ ሰዎች ያዙኝ ልቀቁኝ ባሉ ነበር። በራሳቸው ምስክርነት ይሄው የዝሙት ታሪካቸው። ሙስሊሞችን በመድብለ ጋብቻ ምክንያት ከሚከሱት አንዳንዶቹ ከአንድ በላይ ሚስት ያገቡ ናቸው። ለምሳሌ፡- የሀገራችን ሙስሊሞች እንደ አሸባሪና እንደ ስጋት እዲቆጠሩ በርካታ ጥናቶችን በማዘጋጀት ለመንግስት በማቅረብ የሚታወቀው ዲያቆን ዳኒኤል ክብረት ሁለት ሚስቶች እንዳሉት መምህር ጽጌ ስጦታው በመጽሀፉ *"አንዷና የመጀመሪያ ሚስቱ የባህር ዳር ነዋሪ ስትሆን ከዚች ሚስቱ ትንቢተ የምትባል ልጅ እንዳለችው ሁላችንም እናውቃለን። ... አድስ አበባ ውስጥ ደግሞ ሁለተኛ ሚስት እንዳለችው የማያውቅ ሰው የለም።"* በማለት ጽፏል። (ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 168) ዲያቆን በላቸው የሚባለው የማህበረ ቅዱሳን ሊቀመንበር የነበረ ሰውም ሁለት ሚስቶች እንዳሉት ገልጿል። (ዝኒ ከማሁ፡ገጽ 169) ሌሎችም የክርስትና አባት ነኝ በሚል ስም የአባዋራ ሚስቶች ጋር የሚዳሩ ብዙ ናቸው።

ይሄንን ሁሉ አመንዝራነት ከተራ ምዕመን እስከ ሰባኪዎቿ የያዘች ቤተ-ክርስቲያን ናት ከአንድ በላይ ጋብቻን የምትከለክለው። ለመፈቀዱ በርካታ ማስረጃ የቀረበበትን መድብለ ጋብቻ ክልክል ለማድረግ የማይሆን ድንጋይ ከመንፈቀል ለሰባኪዎቿ ስለ አመንዝራነትና ስለ አምልኮ ስነ-ስርዓት ብታስተምር የሚያዋጣት ይመስለኛል።

ለምን እንደሆነ ግልጽ ባይሆንም በተለይ በቤተ-ክርስቲያኗ በኩል የሚነገሩ የኢትዮጵያ ታሪኮች መሰረታቸው ዝሙት ነው። የንግስተ ሳባ ልጅ ምኒሊክ በዝሙት ነው የተወለደው፡ የንግስት ዮዲት ጉዲት ታሪክ መነሻው ዝሙት ነው፡ እንደ ቤተ-ክርስቲያን ጸሀፊዎች ገለጻ የኢማሙ አህመድ ኢብን ኢብራሒም (አህመድ ግራኝ) ታሪክ መነሻው ዝሙት ነው (አህመድ ኢብን ኢብራሒም፡ ተሾመ ብርሃኑ ከማል፡ ገጽ

22)። በሁሉም የዝሙት ታሪኮች ውስጥ ዋናዎቹ አቀንቃኞች ቄሶች፣ ዲያቆናትና ካህናት ናቸው። ይህስ በቤተ-ክርስቲያኗ ዝሙት እንደተስፋፋ አያመለክትምን?

## ቀላሉ መፍትሔ

መፍትሔው አንድና ቀላል ነው። ገጣሚ መዘክር ግርማ

"ሴቶችን ማሳደግ አቅቶሽ መመዝለግ ሳስተሽ ከጭን ሥር፣

የውስጥሽን ቆሻሻ ታመካኛለሽ በምስር።"

እንዳለው በተለያዩ ሰበቦች ከማመካኘትና ምዕመኑን ለመለጠ ጥፋት ከማጋለጥ በመፅሀፉ የተፈቀደውን መድብለ ጋብቻ መፍቀድና ምዕመናኑን ማስተንፈስ አማራጭ የሌለው ብቸኛ መፍትሔ ነው።

# ማጠቃለያ

ዝሙት በውስጣችሁ ፈልቶ እንደ አሸን

ከተራ እስከ ቄስህ ተላምዶ አመንዝራን

ፓስተር ሀዋሪያህ ነብይህም ሳይቀር

ሲዳራ ሲደፍር ሆኖብህ የሴት ፀር

ስትጠቁም ወደኛ ስትተች ኢስላምን

'ችግር ከገጠመህ አግባ ሁለት ሶስትን'

እጠረጥራለሁ የእይታ ችግርን

ወንጀልህን ቅዱስ አድርጎ የሚያሳይህ

የእስላምን መፍትሔ አድሮ ሚያጠቁርብህ

መነፀር ለብስሃል ወይ እጅግ አሞሀል

ለመዳኒትነት ክፍት አዕምሮና ጥናት ይፈልጋል

አምላካችን አላህ በጥብቅ ያስቀመጠው

መድብለ ጋብቻን መፍትሔ ያረገው

ችግር ያለበትን ይጠቅም ዘንድ ነው

መፍትሄ ነው ብዙ ማግባት

ላሰቃየው የስሜት ሙላት

በአንድ ሚስት መርካት ላልቻለ

ብዙ ማግባት ውስጥ መፍትሔ አለ

ለፈለገ ብዙ መውለድ

ለሆነበት ልጅ ማየት የግድ

ብዙ ያግባ ይውለድ ብዙ

ብሏልና "ብዙ ተባዙ"

ለቺገራት መውጫ መግቢያ

ድህነት ምሱን ላሳያት ፍዳ

ካለህ ትንሽ የሚበቃ

መዘህ አውጣት ከ'ራብ አሮንቃ

አግባት በቃ ደርብና

ሰጥቷል መፍትሔ እስልምና

በስተርጅና ባሏን ላጣች

በብቸኝነት ለተሰቃየች

እንድትወጣ ከቁዘማ

ምናል ብትደረብ ባል ካለማ

መፍትሔ ነው ባል ሲጠፋ

ዝሙት አዳሪ 'ንዳይስፋፋ

የሴት ቁጥር እጅግ በዝቶ

ወንድ ለጫት ተጎልቶ

በሙሉ አገር የሚሰራ ጠፍቶ

አንድ እህትህ ትዳር አጥታ ካለች ከቤት

አቅም ያለው ካገኘህ ድንገት

መፍትሄውን ተጠቀምበት፤

ዘወር በልና ግለጥ መፅሀፍትን

ጋብቻቸውን እይ የነቢያትህን

የአብርሃም የያዕቆም የሙሴ ዳዊትን

ቁጠር የሴት ብዛት ቅዱሳን ሚስቶችን

ሰሎሞን ቢጠበብ ቢመነደግ በውቀት

አግብቶ ነበረ አንድ ሺህ አንድ ሚስት

ከዘፍጥረት ይዘህ ብትሄድ በአዲስ ኪዳን

አንድ ከልካይ የለም መድብለ ጋብቻን

የሚፈልግ ካለ የእውነት መፋረጃ

አንድ አንቀፅ ይፈልግ የመፃ'ፍ ማስረጃ

ብዛት ጋብቻን ገልፆ ሚከለክል

ብዙንም አንሻም አንድ አንቀፅ ይበቃል

አልሆንልህ ካለ አንድም ካላገኝህ

ተጠጋ ወደ እውነት እስልምና አለልህ

ዝሙትህን አዝለህ ከመንቀፍ ኢስላሜን

አውልቅ መነፀሩን ግለጠው አይንህን

ገለጥ ገለጥ አድርግ አንብብ መፅሀፍትን

ትንሽ ያንገላታል መቀበል እውነታን

ግን እመነኝ

ጠልቆ ላነበበ ጠንክሮ ላጠና

እውነት ተሸፍና አትቀርምና

ይገነዘባታል ያውቃታል በቶሎ

መሉ አዕምሮ ያለው ያልሆነ ጎዶሎ።